# የክፉ ቀን አለኝታዋ ትዝታ



## አበራ የማነአብና ገነት ግርማ



-በአበራ ለማ


አንጋፋው የዲሞክራሲና የለውጥ አርበኛ፥ አበራ የማነአብ፥ የሰባ ሁለት ዓመት አዛውንት ናቸው። ከዚህ እድሜያቸው ውስጥ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ባፈላማ ይዟቸው፤ ሃያ አምስቱን ዓመታት ባለም በቃኝና በቃሊቲ ወህኒ ቤቶች ቀርጧቸዋል። ከዚህ ውስጥ ባመክሮ ጥቂት ዓመታት አራግፈው፤ አሥራ ስድስት ዓመት ከስምንት ወራት በሕሊና እስረኝነት አሳልፈዋል። ደሞም ድፍን ሁለት ዓመታትን በጨለማ ቤት በመታገት፤ መራር ግፍና መከራን በመቋቋም፤ ከሞቱት በላይና ከቆሙት በታች በመሆን አቻ እንዳልተገኘላቸው ጉምዡ ትዝታቸው ያረዳናል፡፡

ይህም አልበቃ ያለው አጋች ክፍል አንዲት ጠባብ ክፍል ከሳምባ በሽተኞች ጋር የግድ እንዲጋሩ አድርጎ፤ ለሳምባ በሽተኝነት ዳርጓቸው ኖረዋል። ከዚህ ደዌ ለመፈወስ (ባገር ቤትም ሆነ በቅርቡ እዚህ አውሮፓ ከመጡ በኋላ) አጥብቀው ሕክምናቸውን በመከታተላቸው፤ ዛሬ በሙሉ ጤንነት ላይ ሊገኙ ችለዋል። ለሁለት ዓመታት በካቴና ታስረው እጨለማው ክፍል ውስጥ በሚማቅቁበት ወቅት የጃቸው ቆዳና ሥጋ ተበልቶ አልቆ፤ አጥንታቸው ገጦ ይታይ የነበረበትን የሰቆቃ ዓመታት ሲያስታውሱት እምባቸው ባይኖቻቸው ሙሉ ይሾማል። የኔ ብጤው ሆደባሻ አወያይ ደሞ፤ ሰቆቃቸውን ባይነ ሕሊናው ጭምር እየቃኘ፤ መግቢያ መውጪያው እንደጠፋበት የተከበበ አውሬ ጭንቅ ይለዋል።

"ለመሆኑ እኚህን በምድረ አሜሪካን ከተከበረ ቤተሰባቸው ጋር በሰላምና በተድላ ይኖሩ የነበሩን ትሁት ሰው ምን ተከርቸሌና ተቃሊቲ ወስዶ ዶላቸው?" የሚል መሪ ጥያቄ ያዘለ ሰው ብቅ ቢል አይፈረድበትም። የዚህ መጣጥፍ አቅራቢም ለሥራ ጉዳይ ወደ ቤልጅግ ብቅ ብሎ በነበረበት ወቅት፤ ይህን ጥያቄ ለሞክሼው ለአቶ አበራ ማስቀደሙ አልቀረም ነበር። አካሄዱ እሳቸውንና እሳቸውን የመሳሰሉ ጎምቱ የፖለቲካው ዓለም ምህዋር አርበኞችን የሕይወት ታሪክ "ውርስ" ለተሰኘ የዘጋቢ ፊልም ግብዓት ለመቃረም ነበር። (ይህ ለመጪው ትውልድ ቅርስነት የሚቀመጥ የተንቀሳቃሽ ፊልም ዘገባ አገር ቤትና እውጭ የሚኖሩትን ተጠቃሽ ያገር ልጆችን

አውደ ሰብእና የሚያካትት ነው።) እናም የዚህ መጣጥፍ አቢይ ጭብጥ የሆነው ጉዳይም የተጨለፈው ከዚያው ከታሪካዊው ጭውውትና ቃለ መጠይቅ ላይ እንደሁ ምስጢር ብጤ ላውጣ። የዚህ ሠናይ ሥራ ዋልታና ማገር የሆኑት ባልደረቦቼ ጋዜጠኛና የፊልም ባለሙያው ክብረት መኮንን፥ ረዳቱ ጋዜጠኛ ሥዩም ደገፋ ይሁንታቸውን አይነፍጉኝም በሚል ተስፋም ምስጢሩን ለተደራስያን ሳካፍል ለይቅርታ እጅ እየነሳሁ ነው።

አዎን… ወደ ተነሳው መሪ ጥያቄ ልመለስና "…ሞክሼ እንዲያው ምን እግር ጥሎዎት ለዚህ ዓይነት ዳፋ ተዳረጉ?…" ለሚለው ጥያቄዬ አቶ አበራ የማነአብ የክፉ ቀን ትዝታን ጀልባ እየቀዘፉ፤ ከአሥራ ሰባት ዓመታት በፊት የሆነውን ሁሉ አጫውተውኛል፡፡ በተፈጥሯቸው እርጋታንና ጸጥታን የተላበሰው ገጽታቸው፤ የዘመኑን አንዳንድ ቀዥቃዣ መነኮሳትና ጳጳሳት ያስንቃል። ታንደበታቸው የሚወጣው እጅግ ቁጥብ አስተያየትና ረጋ ያለው ትረካቸው፤ ሲጠጡት ተዋንጫው እንዳያልቅ የሚጨነቁለትንና የሚሳሱለትን የወይን ጠጅ ያህል ያስጎመጃል። ያውም ከጠይም የመልካቸው ቀለም ጋር እየተናበበ… እየተጨዋወተ… እየተሟዘቀ…




ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የተከሳሾችንና የክሱን ዝርዝር ያወጣበት መጽሃፍ

አንጋፋው የመኢሶን አባልና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አዋላጅ ታጋይ አበራ የማነአብ የያኔው የኢድሃቅ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ሲሆኑ፤ የኢሕአፓው መርሻ ዮሴፍ ደሞ ሊቀ መንበር ነበሩ። ታዲያ ታኅሣስ 1986 ዓመተ ምህረት

አዲስ አበባ ላይ በግዮን ሆቴል የሚካሄድ "የሰላምና የእርቅ ጉባዔ" በኢድኃቅ ይዘጋጃል። የዝግጅቱ ሊቀመንበርና አስተባባሪም ዶ/ር ነገደ ጎበዜ እንደነበሩና የእዝ ማእከላቸውን አውሮፓ ላይ አድርገው ለዝግጅቱ ከፍተኛውን ድርሻ ይፈጽሙ እንደነበር በጭውውታችን ጊዜ ልረዳ ችያለሁ። የዚህን ጉባዔ እውን መሆን በጉጉት ይጠብቁ የነበሩት እነአቶ አበራ የማነ አብ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ለጉዞ ሰነቁ። አዲስ አበባ ላይ ተገኝተው ወያኔ/ኢሕአዴግን በዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ አገባብ አንበርክከው ያገሪቱን ሰፊ ሕዝብ የልብ ትርታ ያደመጠ ሥርዓት ሊገነቡ ወደ ሸገር ገሠገሡ።

| ሐ. ከ20 እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት የተቀጡ የደርግ ተከሳሾች | | |
|---|---|---|
| 3 | አበራ የማነአብ ጊላይ | በከ/ልማት የማህበራት ማ/መምሪያ ኃላፊ |

ለዚህ ሠናይ አገራዊ ጉባዔ በሉፍታንዛ አውሮፕላን ታሜሪካን የተንቀሳቀሱት፣ አበራ የማነአብ፥ ሥዩም ዘነበ፥ መስፍን ተፈራና ገነነው አሰፋ ሲሆኑ፤ ፍራንክፈርት ጀርመን ላይ አውሮፕላኑና አብራሪዎቹን አስቀይረው፣ የስዊድኑን ዓለማየሁ ዴሬሳንና የፈረንሳይዋን ነዋሪ ገነት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስን አዳብለው ወደ ሸገር በረሩ። እግረ መንገዳቸውንም እነ አቶ መርሻ ዮሴፍን በዚያው በተሳፈሩበት አውሮፕላን ለመቀላቀል አስቀድሞ በታቀደው መሠረት ካይሮ ላይ ቆይታ አደረጉ፡፡ እናቶ መርሻን የበላ ጅብ ያልጮኸበት ምክንያት ሳይታወቅ ቀረና ብቻቸውን እንደቆዘሙ ወደ ሸገር አቀኑ። በጋራም ሆነ በተናጠል የኢድሃቅ ጓዶቻቸውን ምን እንደዋጣቸው ከመጣላቸው መላ ምት ጋር እንደተፋጠጡ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደረሱ።

በታዳጊ ሕጻናት እቅፍ አበባ አሲዘው ቦሌ ላይ ሊቀበሏቸው ብቅ ያሉ "የሰላምና የእርቅ ጉባዔ" አዘጋጆች ሳይሆኑ፤ ተቀራኒዎቹ ሆኑ። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የጸጥታ ሠራተኞች በካቴና እጅ እጃቸውን እያሠሩ ወደ "ማረፊያ ቤት" ወሰዱዋቸው፡፡ ውሎ አድሮም፤ የጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ "**ደም ያዘለ ዶሴ**" በሚል ርእስ በ2002 ዓ.ም. ባሳተመው ዳጎስ ያለ መጽሃፍ ላይ አቶ አበራ የማነአብ የ25 ዓመት ጽኑ እስራት እንደተፈረደባቸው ያረጋግጣል።

አዎን… ታጋይ አበራ የማነአብ ያንን ዱብዳና ቀውጢ ወቅት እጅግ በመረረ ሃዘንና ቅይምታ ያሳታውሱታል። ላገርና ለወገን አንዳች ቋር ያለው ቁም ነገር ለመሥራትና ቤዛ ለመሆን እንጂ፤ ውበትና ብርሃንን ብቻ ተማላበት ተነበልባሉ ተተዶለችው የሳት እራት ለመማሰል እንዳልነበረ አሁን ላይ ሁነው ሲያስቡት በእጅግ እጅጉ ይቆጫሉ። እናም እሳቸውና ጓዶቻቸው ከታገቱ በኋላ "መንግሥትን በኃይል ለመገልበጥና ጦርነት በማወጅ" በሚል ዐቢይ ክስ ፍርድ ቤት ቀረቡ። ተከሳሾቹ አበራ የማነአብ፥ ገነት ግርማ፥ ሥዩም ዘነበ፥ መስፍን ተፈራና ገነነው አሰፋ ነበሩ። ዓለማየሁ ዴሬሳ የስዊድን ዜጋ በመሆኑ አምባሳደሩ መጥቶ ስላስፈታው እሱና አንድ ሌላ ሰው ከክሱ ነጻ ሊሆኑ መቻላቸውን የሕሊና እስረኛው አቶ አበራ ያስታውሱታል።

ቦሌ ላይ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅርና አዘኔታ እንዳልተለያቸው ምስጋናን አንተርሰው ያወሳሉ። ባገር ውስጥና በውጭ የሚኖረው ወገን ሁሉ ለሰላምና እርቅ ፍለጋ መጥተው እንዲህ ያለ አሳዛኝ እንግልትና እስር ላይ መውደቃቸው ፍትሃዊ አለመሆኑን በመግለጽ ኢሕአዴግን መፈታተኑን አቶ አበራ ያሰምሩበታል። እናም ከሕዝብ፥ ከዲፕሎማቲክ አካላትና ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ጭምር እጅግ ጫናና ውትወታ የበዛበት ወያኔ/ኢሕአዴግ በስተመጨረሻው አንድ አቋም ላይ መድረሱን አቶ አበራ የማነአብ ያወሳሉ። ፍርድ ቤቱ ከበላዮች በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ካቶ አበራ የማነአብ በስተቀር ሁሎቹንም በነጻ ለቅቄያለሁ ሲል ብይን ይሰጣል። ያቶ አበራ ጓዶች የነሱ ስም ተጠርቶ ያቶ አበራ ስም ሳይጠራ በመቅረቱ ግር ይላቸዋል። ምናልባት ዳኛው በስህተት ዘለዋቸው ይሆናል በሚል እምምታ "አበራ የማነአብስ?" ሲሉ ዳኛው ላይ ያፈጡባቸዋል። ዳኛው፤ ፍርድ ቤቱ አቶ አበራን በእስር ለማቆየት መወሰኑን ያረዷቸዋል። ይሄኔ ያቶ አበራ የቁርጥ ቀን አራቱም ጓዶች፤ ገነት ግርማ፥ ሥዩም ዘነበ፥ መስፍን ተፈራና ገነነው አሰፋ በሕብረትና ባንድ ቃል "ይሄማ የማይደረግ፥ የማይሞከር ነው!… አበራ የማነአብ ማለት እኛ፥ እኛ ማለት አበራ የማነአብ ነን!… ይፈታልን!…." ሲሉ ፍርድ ቤቱን ቀውጢ ያደርጉታል።

እንዲህ ያለ ሕብራዊ አንድምታ ይመጣል ብለው ያልጠበቁት ዳኛ ግራ እንደተጋቡና የሚሰጡት ምላሽም እንዳጡ አቶ አበራ ያንን የችሎት ቀን እየተከዙ ነበር ያስታወሱልኝ። እነገነት ግርማ ግን በዚህም አልበቃቸውም ይላሉ። "ዳኛው ከሰጡት ብይን እንደማይፈናፈኑ ሲረዱ እኔ ላይ ተጠምጥመው እሪታቸውን አቀለጡት።

*እጅግ እጅግ መሪር ልቅሷቸውን ከመሪር የመጥፎ ሥርዓት እርግማንና ውግዘት ጋር አሳጅበው በችሎቱ ላይ አመጹ። አበራም ከኛ ጋር ካልተፈታልን ሞተን እንገኛለን!... ሲሉ ለነጻነቴ ከራሳቸው በላይ ሁነው ቆሙልኝ..." ሲሉ እምባ እየተናነቃቸው የኒያን የክፉ ቀን ቁርጥ ጓዶቻቸውን ውለታ በታላቅ አድናቆት፥ አክብሮትና ምስጋና አጫውተውኛል ሞክሼ። ፍርድ ቤቱ ባልተለመደ አመጽና እምቢ ባይነት ሲደፈር አይተው የማያውቁት ሕግ አስከባሪዎች፤ የዳኛውን የ"ጸጥታ ይከበር" ቀጭን ትእዛዝ በቃልም፥ በግልምጫም፥ በጥቅሻም ቢኸርጎደጎድ አራቱን አንበሶች የሚበግር አልሆነም።*



*አንጋፋው ታጋይ አቶ አበራ ከክራራቸው ጋር*

*እናም በመጨረሻው ዳኛው እራሳቸው አስቀድመው ችሎቱን ለቀው መውጣት ግድ እንዳላቸው በሥፍራው የነበሩ ሌሎች ታዛቢዎችም ለዚህ ጸሐፊ ያጫወቱት ትዝ ይለዋል። እናም አቶ አበራ መራር ትዝታቸውን እንዲህ ሲሉ ቀጥለውበታል።*

*"....ጓዶቼ ተችሎት እየተጎተቱ ወደነበሩበት ወህኒ ቤት ሲመለሱ አንዳቸውም ከልቅሶና የኢሕዴግን መንግሥት አምርረው ከማውገዝ የተቆጠቡ አልነበሩም። ወህኒ ቤት ስንደርስ እቃቸውን ቶሎ ቶሎ ሸክፈው እንዲወጡ የወህኒ ቤት ፖሊሶች ሲያጣድፏቸው፤ የኔ ጓዶች ግን በተረበሸ መንፈስ ውስጥ ሁነው ልቅሷቸውን እንደቀጠሉበት ነበር። እኔን እዚያ ጥለው መፈታት ጨርሶ የማይታመን ሁኖባቸው፣ የሚያደርጉት መላ ቅጡ ጠፍቶባቸው፣ የትውልዳችንን እጣ ፈንታ ጥርስ በሌለው አንበሳነት እልክ ውስጥ አስገብተው፤ በእምባ ዘለላቸው እያዘከሩት ነበር። እናም አለቀሱልኝ... እናም በልባቸው ቆሰሉልኝ... አንዲት የነጻነት ቀንንም ተመኝተውልኝ፤ በወህኒ ፖሊስ ትእዛዝ እየተጠደፉ ተለዩኝ..." ያላሉ አንጋፋው የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ታጋይና አርበኛ አበራ የማነአብ።*

*አዎን... ወንዶቹ ታሣሪ ጓዶቻቸው እሳቸው ከነበሩበት ወህኒ ቤት ሲፈቱ እያለቀሱ ተለዩዋቸው። "ያቺ ብቸኛ የትግል ጓዳቸው ሴቷ ገነት ግርማስ እንዴት ሁና ይሆን?..." የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ልክ ነው፣ ተገቢም ጥያቋ የመሆኑን ያህል ተገቢም መልስ አቶ አበራ የማነ አብ አላቸው። "... ገነት!? ገነትማ ከችሎቱ እንደወጣን እሷም እንደወንዶቹ ጓዶቼ ሁሉ እያለቁሰች ወደ ሴት እስረኞች ክፍል ተመለሰች። እናም እዚያ ያሉትም የወህኒ ፖሊሶች ገነት እቃዋን ሸክፋ ባስቸኳይ እስር ቤቱን ለቃላቸው እንድትወጣ ያጣድፏታል። ገነት ግን መሪር ሃዘኗን በእዬዬዋ ከመግለጽ ባሻገር የፖሊሱን ትእዛዝ የምትሰማም የምትፈጽምም አልነበረችም። ወዲህ ወዲያ እየተንጎራደደች በሃዘን ወለሌ ትላለች። የኔን አሳዛኝ መጨረሻ እያሰበች ታልቅስልኛለች፥ ትጮህልኛለች... ይፈቱኝም ዘንድ ያገር ያለህ የወገን ያለህ.... ትላለች። ልቅሶዋ ልቅሶው የሆነ ጩኸትዋ ጩኸቱ የሆነ አንዳች ወገን ባካባቢው ጠፋ። እናም ወህኒ ቤቱን ለቅቄ አልወጣም ብላ አመጸች። ይሄኔ ትልቅ ረብሻ ተነሳ..." ይላሉ ሞክሼ።*

ከተራ የወህኒ ፖሊስ አንስቶ እስከ ባለማእረጎች ድረስ እየተፈራረቁ ጀግናዩቱን የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ታጋይ እታለም ገነት ግርማን "ወህኒ ቤቱን ለቀሽልን ካልወጣሽ በጃችን ሰበብ ትሆኛለሽ..." የሚል እልክ አስጨራሽ ሙግት ይገጥሟታል፣ ያስፈራሯታል። የታለም ገነት መልስ ግን አንድና አንድ ብቻ ነበር። “እምቢ!!”

“ንጹሁ አበራ ካልተፈታ ወህኒ ቤቱን ለቅቄ አልወጣም!!!"

“ዋ... በሕይወትሽ ላይ መፍረድሽን እውቂው...”

"የኔ ሕይወት ካንድ ንጹህ ዜጋ ሕይወት በላይ አይደለምና የፈለጋችሁትን ልታደርጉኝ ትችላላችሁ... "

"እኛ ትእዛዝ ፈጻሚዎች ነን... ባስቸኳይ አስወጧት ተብለናልና በግድሽ ትወጪያታለሽ..."

"አልወጣም ብያለሁ!... አልወጣም!... አሁንም አበራ ካልተፈታ አልወጣምና የምታደርጉኝን ሁሉ በጸጋ እቀበላለሁ!"

ይህን መሰል እልክ አስጨራሽ ምልልስና ጭቅጭቅ ለረዥም ሰዓቶች በቆራጧ ታጋይ በወይዘሮ ገነት ግርማና በወህኒ ቤት ፖሊስ ወታደሮችና አለቆች መካከል ሲካሄድ ቆየ። ግና አንዳችም ለውጥ ሳይመጣ የበላይ አካል ትእዛዝ ሳይፈጸም ሊቀር ሆነ። የወህኒ ፖሊሶች ከታች እስከላይ ፈተና ላይ ወደቁ። "አጅሪት ማንንም የማታስቀርብ የቆሰለች አራስ ነብሪትን ሆነች" ያላሉ እጅግ ጭምቱና ባለስስ መንፈሱ አበራ የማነአብ ትክዝ ብለው።



ቆራጥዋ ታጋይ ወ/ሮ ገነት ግርማ

አንበሲት ተነብሯን ምንም ምንም ማድረግ ያቃታቸው የወህኒ ቤቱ ጥበቃ ሃላፊዎች የማታ ማታ አንዳች መላ ሲያባንናቸው፤ አቶ አበራ የማነአብ ወደታሰሩበት የወንዶች ምድብ ክፍል ባጀብ ይመጣሉ። አቶ አበራንም አስጠርተው፤ ወይዘሮ ገነትን ከወህኒ ቤት ማውጣት እንዳቃታቸውና እርሳቸው የሚቻላቸውን ትብብር እንዲያደርጉላቸው ይማጸኗቸዋል። እኒህ ደም ደም ያላቸው ያመረሩ ታዛገሮች "እርሶም የማይተባበሩን፣ እሳቸውም አቋማቸውን የማያስተካክሉ ከሆነ የኃይል እርምጃ ልንወስድ እንገደዳደለን!... ከሕግም ከህሊናም እዳ ተጠያቂነት ነጻ መሆናችንን እንዲያውቁልን!!!...." ሲሉ ጫን ባለ ኃይለ ቃል ቁርጡኛ ውሳኔያቸውን ላቶ አበራ ያሳውቋቸዋል። እጅግ ትእግስተኛውና አርቆ አሰተዋዩ አበራ የማነአብ የነገሩ እያዎነት (PARADOX)

እያስገረማቸው፤ የፖሊሶቹን ምጻኔና ሊወስዱ የፈለጉትን የኃይል እርምጃ ባይነ ሕሊናቸው አገላብጠው ካዩት በኋላ፤ የታለም ገነት ሕልውና ከማንም ከምንም በላይ ሆኖ ይታያቸዋል። ጊዜ ማጥፋትና ሌላ ሌላ የሰይጣን ጆሮ ሊሰማው የሚችል ክፉ ነገር ታክሎ እንዲነገራቸው አልፈለጉም።

"ምን ልርዳችሁ? ምን እንድተባበራችሁስ ትፈልጋላችሁ? እባካችሁን ያሻችሁን ጠይቁኝ..." እያሉ አቶ አበራ በተራቸው ፖሊሶቹን መማጸናቸውን የዘወትር መተከዣቸው የሆነችው ክራራቸውን እየደባበሱ አጫወቱኝ። ክራር ጨዋታን ቃሊቲ እያሉ መማራቸውን እዚህ ላይ ልብ ይሏል። በነገራችን ላይ የትግል ጓዳቸው ዶ/ር ነገደም ድንቅ ክራር ተጫዋችና አንጎራጓሪ መሆናቸውንም በዚህ አጋጣሚ አስተውያለሁ።

"እኛማ... እኛማ እርስዎን ልናስቸግርዎት የፈለግነው፤ ጓደኛዎ ወይዘሮ ገነት እርስዎ ካልተፈቱ በስተቀር ወህኒ ቤቱን ለቅቄ አልወጣም ስላሉን፤ መጥፎ ደርጃ ላይ ከመዳረሳችን በፊት እርስዎ እራስዎ ለምነው እንዲያስወጡልን ነው..."

" እሺ ... ምን ገዶኝ በደስታ ነው እንጂ የምተባበራችሁ..." ሲሏቸው የወህኒ ፖሊሶቹ የሰሙትን ማመን እንዳቃታቸውና እጅግ እንደተደሰቱ አቶ አበራ በትዝብት ያስታውሱታል። የሳቸው ሙሉ ትብብር እታለም ገነትን ካደጋ ለመታደግ እንጂ እነሱና አለቆቻቸው ንጹሁን እሳቸውን በግፍ የበየኑባቸውን እስር አሜን ብለው መቀበላቸው እንዳልሆነ ምጸቱ እንዲገባቸው አንዳች መልአክ ወይም ሰይጣን በልቡናቸው ሹክ ቢላቸው በፈቀዱ ነበር። ግን አልሆነም። በእስር ረዥም ዘመናቸው በሳንባ በሽታ እንዲሠቃዩ፥ ከሁለት ዓመታት በላይ በእግር ብረት ታስረው ጽኑ የጨለማ ቤትን ቅጣት እንዲቀበሉ "ተስማምተው"፤ የተጠየቁትን ትብብር እሺ ብለው ጓዳቸውን ወ/ሮ ገነትን ለመለመን ወደ ሴቶች እስር ቤት ተከትለዋቸው ሄዱ።



አቶ አበራ ከሴቶቹ እስር ቤት ሲደርሱ ወይዘሮ ገነት በንዴትና በሃዘን በግነው፤ የራስ ዳሽንን ተራራ ያህል ተከምረው፤ ባንበሲት ነብሪት ግርማ ሞገስ "ማን አባቱ ይጠጋኝና!..." እያሉ ሲፎክሩ፥ ከእልክ ሲቃቸው ጋር ሲታገሉና ሲያለቅሱ ያገኙዋቸዋል። እጅግ ትሁቱና ሰው አክባሪው አቶ አበራም ተጠግተው "እባክሽን"ን ያስቀደመ ልመናቸውን ያቀርባሉ።



"...ገንዬ እባክሽ ተለመኚኝ... መንግሥት ደስ ያለውን በኔ ላይ ለማድረግ ወስኗል። ባንቺ አቅምና ጉልበት ለኔ ያለሽን ሁሉ በእምባሽ ጭምር ገልጸሽልኛል። ፍትህን ማግኘት ካንቺም ከኔም አቅም በላይ ነው። ምንም ለውጥ ማምጣት በማንችልበት ሁኔታ ውስጥ እያለን፣ ምንም ዓይነት ጉዳት ባንቺ ላይ እንዲደርስ አልፈልግም። እባክሽ ይህን መጥፎ ቦታ ለቀሽላቸው ሂጂ... እኔ እንደፈረደብኝ እወጣዋለሁ..." ሲሉ ይማጸኗታል።

“እንዴት ብዬ ጥዬህ እወጣለሁ? አልወጣም!... ያለወንጀልህ ስትሰቃይ እያየሁና ንጹህ ሕሊናዬ እየሞገተኝ እንዴት ብዬ?..." እጄዬዋን ታቀልጠዋለች። አቶ አበራም በዚያ ገራምና ትሁት እንደበታቸው አሁንም አጥብቀው የእሷ ያላንዳች አደጋ ከዚህ ክፉ ቦታ መውጣት ወሳኝ ደረጃ ላይ መድረሱን ያስረዷታል። የወህኒ ፖሊሶቹ ትእዛዝ ፈጻሚዎችና ለእንጀራቸው ታዛዦች መሆናቸውና ረጋ ብለው አስረዷት። ሂዶ ሂዶም ታዛዦቹ ግዳጃቸውን ለመፈጸም የግድ ትእግስታቸውን ስለሚያሟጥጡ፣ ግዳጃቸውን ክፉ መልክ ባለው ድርጊት መፈጸማቸው ስለማይቀር፣ እንድትተባበራቸው በጽሞና አስረዷትና የማታ ማታ ልመናቸውን ተቀብላ እምባዋን እያዘራች ከወህኒ ቤቱ ተሰናብታቸው ወጣች።

እታለም ገነት ከእልክ አስጨራሹ የወህኒ ቤት ሙግትና እምቢባይነት በኋላ ግቢውን ለቃ ብትወጣም፣ ካቶ አበራ የማነአብ ሕሊና ውስጥ ግን ዘላለሚን ጎጆዋን ሠርታ ቀርታለች። ስለሷ ታላቅ ሰብእናና የቁርጡ ቀን የእውነት እውነት አብሮነት የሕሊና እስረኛው አቶ አበራ የማነአብ አውግተው አይጠግቡም። እንዲያውም ወደኋላ መለስ ብለውም በሳቸው ድርጅት በመኢሶንና በነወይዘሮ ገነት ድርጅት በኢሕአፓ መካከል የነበረውን የብዙ አሠርት ዓመታት የ"ባላንጣነት" ስሜት ወደ ጨዋ የሰለጠነው ዘመን የፖለቲካ "ወዳጃምነት" የመለሰውን መልካም አጋጣሚ ባድናቆት ያስታውሱታል::

አቶ አበራ "የቶሮንቶ ጉባዔ" እየተባለ ከሚጠቀሰው የ1982 ዓ. ምቱ ጉባዔ ወቅት ጀምሮ በብዙ አገራዊ ጉዳዮች ላይ መኢሶንና ኢሕአፓ ተቀራርበው አብረው መሥራት መጀመራቸውንና የጋራ ጠላትን አንገት ማስደፋታቸውንና ወዳጆቻቸውን ደሞ ጎሽ ማሰኘታቸውን ያወሳሉ። ከዚያ ጉባዔ በኋላም ኢድሐቅ እንዲመሠረት ሁለቱ ድርጅቶች ያንበሳውን ድርሻ ሚና እንደተጫወቱ አቶ አበራ ያስታውሳሉ።

የዚያ ሁሉ ያብሮነትና የመቀራረብ ውጤት እታለም ገነት ግርማን፥ ባለቤቷን አቶ ኢያሱ ዓለማየሁንና ብዙ የኢሕአፓ አባላትን በወዳጅነት ለማትረፍ እንዳስቻላቸው አቶ አበራ በእጅጉ ያሰምሩበታል። ተከሰው ፍርድ ቤት በቀረቡበትም ወቅት፣ ካቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮች መካከል የኢሕአፓ አባላት የሆኑ ሁለት ጥንዶች እንደሚገኙበት አጫውተውኛል። እኒህ ጥንዶች ያቶ አበራን ኀጽህናና ታላቅ ሰብእና በመመስከር፣ ከእስር በነጻ እንዲፈቱ ብርቱ እማኝነትን የሰጡላቸው እንደነበር በምስጋናና ባድናቆት ይገልሱታል።

ዛሬ በሕይወት የሌለውንና ባንድ ክፉ ቀን የደርግ ሰለባ ሆኖ የቀረውን የድርጅታቸውን ቁልፍ ሰው የኃይሌ ፊዳንና፣ ዛሬም በሕይወት ያሉትንና ቤልጅግ ላይ አብረው ያገኟቸውን የዶ/ር ነገደ ጎበዜን አንድ ሕልምም ተፈቶ ማየታቸውን ጫዋታችን ላይ አልሸሸጉኝም። እኒህ ሁለት ተጠቃሽ ጓዶቻቸውና ሌሎቹም የድርጅታቸው ቁልፍ ሰዎች ሁሉ፣ አንድ ቀን እንደ ኢሕአፓ ከመሳሰሉ አቻ ድርጅቶች ጋር መተኪያ ለሌላት ለዚቹ እናት አገራችን ጎን ለጎን ቆመን የምንታገልበትና ለወገኖቻችንም ቤዛ የምሆንበት ቀን ይመጣ ይሆናል ሲሉ እንደነበር በአንክሮ ያስታውሱታል።

አዎን… የታለም ገነት ዓይነቱ የወህኒ ቤቱ አቻ ያልተገኘለት የክፉ ቀን አለኝታነት ተሞክሮና ተገብሮ፤ የናቶ ኃይሌ ፊዳን ረዥም ሕልም ለመፍታት ማልዶ የታየ የንጋት ኮከብነት ተምሳሌ ያለው አኩሪ ተግባር ነው። ያ መንፈስ አሁንም ጠንክሮና ጎልብቶ አገራዊ ልብን የሚገዛና አኩሪ ትውልድን ባኩሪ የታሪክ ጀልባ ላይ አሳፍሮ የሚያሸጋግር እንዲሆን መጣር ያስፈልጋል። በሕብረቱ ያብሮነት ጉዞ ዘመን ሸግኖ የነበረው መናበብ፤ ዳግም እንዲታደስ የግድ ይላል::

ላቶ አበራ የማነአብና ለታለም ገነት ግርማ ረዥም እድሜና ጤናን እመኛለሁ። እኔና የሙያ ባልደረቦቼ በጥልቀት የሂድንበትን አውደ ሰባዊ የተንቀሳቃሽ ምስል ዘገባ "ውርስ" በተሰኘው ጥናታዊ ዝግጅታችን ውስጥ እስክናቀርበው ድረስ፤ ሁለቱም በያሉበት በደህና ይቆዩልን። ደሞም ሁለቱም ለትውልዱ "ውርስ" ዝግጅት መጣኒና ብቃት ያላቸው ተመራጮች በመሆናቸው እንኳን ደስ ያላችሁ ስንላቸው መንፈሳዊ ኩራት ይሰማናል። ከሌሎች አከል ያገር ልጆች ጋር ታድመው ለመጻዒው ትውልድ ቅርስነት፤ በ"ውርስ" መንኮራኩርነት ከያለንበት አምባ የሚደርሱበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።



መስዋዕቱ  አቶ  ኃይሌ ፊዳና የትግል ጓዳቸው ዶ/ር ነገደ ጎበዜ እ.አ.አ. በ70ዎቹ አሠርት ዓመታት መጀመሪያ ላይ በምሥራቅ በርሊን

አቶ አበራ በቅርቡ ወደ አሜሪካን ተጉዘው ከሁለት ልጆቻቸውና ከውድ ባለቤታቸው ጋር በሰላም ይገናኙ ዘንድ ያምላክ ቸርነቱ ይሁን።

*ለአስተያየት ዎ…* ***ablemma@gmail.com***